# ታላቅ አገር፤ትንሽ መንግሥት

በኦሪት ዘፍጥረት፣ በምዕራፍ ሁለት
እግዚአብሔር ሲፈጥር፣ የምድርን ገነት
ኤደንን የሚዞረው፣ እንደመቀነት
የግዮን ወንዝ ነው፣ ከኢትዮጵያ መሬት
ይኸ ምስክር ነው፣ የጥንታዊነት፡፡

በሳይንስም ቢጣራ፣ የሰው መሠረቱ
በአዝጋሚ ለውጥ theory፣ ቢደረግ ጥናቱ
ሁሉም የሚያሳየው ወደ፣ አንድ አቅጣጫ ነው
ያችኑ ኢትዮጵያን፣ የLucyን አገር ነው፡፡

ታላቋ ኢትዮጵያ፣ ጥንታዊት ምድር
የአፍሪካ የዓለም፣ ቤተ መዘክር
የጀግና ሕዝብ እናት፣ የእምነት ደብር
ማን አለ እንደ እሷ፣ ቢፈለግ ቢዞር፡፡

የአውሮፓ ኃያላን፣ አፍሪካን ሲጋሩ
ሰዉን እንደእንስሳ፣ ሲፈቱና ሲያስሩ
ኢትዮጵያ ብቻ ናት፣ ተከብራ የኖረች
በልጆቿ ገድል፣ ፋሽስት ያባረረች፡፡

ታሪካችን አኩሪ፣ ስማችን ገናና
እንደኛ አይነት ሕዝብ፣ ከቶ የት አለና!

በአፍሪካ ብቸኛው፣ ግዕዝ ፊደላችን
በዓለም ላይ የሌለው፣ ደቃቁ ጤፋችን
Coffee የተባለው፣ የከፋው ቡናችን
የማራቶን ሩጫ፣ የዓድዋው ድላችን
የዳሸን ተራራ፣ የሰምጥ ሸለቋችን
የሥልጣኔው ምንጭ፣ የአባይ ወንዛችን
የOAU Office፣ በአዲስ አበባችን
ይህንን ይመስላል፣ አኩሪው ታሪካችን
ታላቅ አገር አለን፣ ታላቅ ነው ሕዝባችን፡፡

ታዲያ ለታላቅ ሕዝብ፣ መንግሥት የሆነው
የወያኔ አገዛዝ፣ ጠባብ ዘረኛው
በረሃብ በጦርነት፣ ሕዝቡን ሲፈጀው
ለመብት ተሟጋቹን፣ ቃሊቲ ሲያስረው
ያልታጠቀን ዜጋ፣ ግንባሩን ሲለው
መሀይሙን ደሀ ሕዝብ፣ ፍዳ ሲያበላው
በከፋፍለህ ግዛ፣ ሲያተራምሰው
አገር ሲያል፣ ስትሆን በአጋዚ ጦር
ዝምታ አይበጅም፣ ኅበዝ ተጋተር፡፡

በሰላም በምርጫ፣ በደንቡ ካልሆነ
በሀይል በጠብመንጃ፣ በቦንብ ከታመነ
እዛ እሳት ካለ፣ እዚህም እሳት አለ
የመንግሥት ትንሽን፣ የሚወደው የለ፡፡

አሳፋሪ መንግሥት፣ የመንግሥት ትንሽ'
የMafiaዎች Group፣ የነግድ የለሽ'
የጭካኔ ተቋም፣ የአድርባይነት'
ጨርሶ ጠላት ነው፣ የኢትዮጵያዊነት፡፡

ፋሽዝም ናዚዝም፣ በኢትዮጵያ ሲነግስ'
በዘመኑ ሂትለር፣ በአቶ መለስ'
የሰው ካባ ለብሶ፣ በእባብ ተመስሎ
አበሻን አፍኖ፣ ነጮቹን አታሎ
እስከመቸ ይሆን፣ የሚኖረው ቀሎ?

በጣም ያሳፍራል፣ በኢትዮጵያ የመጣ
በታላቅ ሕዝብ ላይ፣ ፀረ ሕዝብ ሲወጣ
ዲሞክረሲ ሲሞት፣ ነፃነት ሲቀጣ
ጨለማው ሲራዘም፣ ፀሐይ እንዳትወጣ፡፡

መብትና ነፃነት፣ የሚከበርባት
ፍትህ እኩልነት፣ የተንሰራፋባት
ሰዉ እንደዶሮ፣ የማይታሰርባት
ፍርሃትና ስጋት፣ የተወገዱባት
ሰላም ዲሞክራሲ፣ ጎልተው የሚታዩባት
እኔ የምሞትላት፣ ኢትዮጵያ ይህች ናት፡፡

ከሣህሉ በቀለ (ቶሮንቶ)